## ***ኢሕአፓ በአዲስ አበባ የቅስቀሳ በራሪዎችን መበተኑን ቀጥሏል***

***ከጥር 17 ጀምሮ እስካዘሬ ድረስ ኢሕአፓ ቀስቃሽ በራሪዎችን በአዲስ አበባ መበተኑን መቀ ጠሉ ተዘገበ ። ይህ ቀጣይ እንቅስቃሴ ወደ ሌሎች ከተሞችም የሚስፋፋ መሆኑንም ማወቅ ተችሏል።***

***የተበተኑት ወረቀቶች የኢሕአፓ ጥሪ ለተማሪና አስተማሪ፤ ለጦር ሀይሎች፤ የወክንድ ጥሪና ሌሎችም ወቅታዊ መልዕክቶች ናቸው። በራሪዎቹ የተሰራጩት በአራት ኪሎ፤ በስድስት ኪሎ፤ በአምስት ኪሎ፤ በካዛንቺስ፤ በጦር ሀይሎች፤ከርቸሌ፤ሰሜን ሆቴልን ይዞ እስከ ጊዮርጊስ ፒያሳ፤ መርካቶ፤ አውቶቡስ ተራ፤ አየር ጤና፤ ገብረክርስቶስ፤መገናኛ፤ ቦሌ፤ ሀያ ሁለት፤ ሰንጋ ተራ፤ ተክለ ሀይማኖት፤የካ፤ ጉርድ ሾላ፤ቀበና፤ሚኒሊክ ሆስፒታል፤ስታዲዮም፤ ብሔራዊ ቲያትር፤ለገሀርና ሌሎችም አካባቢዎች ነው። ሕዝብን በተለይም ወጣቱን ክፍል ለሕዝባዊ አመፅ የሚጠሩት የኢሕአፓና የወክንድ መልዕክቶች በፍኖተ ዴሞክራሲ ራዲዮ የተደመጡ ቢሆኑም በበራሪ ደረጃ መተላለፋቸው ሰፊ ስርጭትና ተጨማሪ አንደምታ እንደ ሚኖራቸውም ግልፅ መሆኑ ተነግሯል።***

***ኢሕአፓ በከተሞች በይፋ እያደረገ ያለው እንቅስቃሴ በቂ ጥናትና ዝግጅትን ተከትሎ የመጣ በመሆኑ ለአደጋ የሚያጋልጥ ሆኖ አልተገኘም። የበራሪ ወረቀቶች ብተናው በተለ ይ ሕዝብን ለአመፅ ጋባዥ ናቸውና ውጤታቸው ለትግሉ ጠቃሚ መሆኑ አያጠራጥርም። በተጨባጭ ትግል እንተባባር የሚለው የኢሕአፓም ጥሪ በሰሞኑ በአዲስ አበባም ተሰራጭቷ ል። ድርጅቱ ለዚህ ተግባራዊ ምላሽ በመጠበቅ ላይ ያለ ቢሆንም በራሱ ግን ሕዝብን መቀስ ቅሱንና ለወሳኝ ፍልሚያም መዘጋጀቱን ችላ አላለም። ሰሞኑን በአዲስ አበባ በኢሕአፓ ከተሰራጩት ልዩ ልዩ በራሪዎች/ መልዕክቶች አንዱ ከዚህ ቀጥሎ ሰፍሯል--***

## ሊፈነዳ ለተቃረበው ህዝባዊ አመጽ እንዘጋጅ

አምባገነኖች የጭቆና ዘመናቸውን ለማራዘም የደህንነት፣ የፖሊስ፣ የጦር ኃይልን አግዝፎ በማራጀት የህዝብን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በመጨፍለቅ ደይን ጭቆናን የማስፈን የጋራ ባህርይ አላቸው። ህዝብ የተጫነበት ጭቆና ጫናው በበረታ ቁጥር በተለያ ጊዜና ቦታ እምቢኝ ብሎ በጠበንጃ የተነጠቀውን መብቱን ለማስከበር ነፃነቱን ለመቀዳጀት አምጾ መነሳቱ የነበረ፣ አየተደረገ ያለና ወደፊትም የማይቀር ሀቅ ነው። በቱኒዚያ ሆነ በግብጽ በቅርቡ ከተከሰቱት አገር አቀፍ አመጾች በፊት በተለያዩ ዘመናት በተለያዩ የህብረተ ሰብ ክፍሎች የየገዢዎቹን ጭቆና በመቃወም እንቅስቃሴዎች የካሄዱ እንደነበር ከታሪክ ማህደር መገንዘብ ይቻላል። በሁለቱም አገሮች ለተከሰቱት ጠንካራና አይበገሬ ህዝባዊ አመጾች የጥንካሬያቸው ምንጩ በጋራ ጠላት ላይ በህብረት በአንድ ላይ መቆሙ ብቻ ነው። የግብጽ አማጽያን ደጋግመው ያስተጋቡ የነበረው ሙስሊምም

ሆን ክርስቲያን፣ ሰሜንም ኖርን ደቡብ፣ ምስራቅም ኖርን ደቡብ ግብጻውያን ነንና የሙባረክ መንግስት ጭቆና በሁላችም ላይ በመሆኑ በአንድ ላይ እንቁም የሚለው ትልቅ ድርሻ ነበረው፡፡ ይህን መልእክት እኛም ልንጋራው ይገባናል፡፡

በወያኔ 20 የጭቆና ዘመናት በተለያዩ ጊዜያትና ቦታዎች አምባ ገነኑን የጥቂት ዘረኞች መንግስትን በመቃወም ህዝባዊ እቅስቃሴዎች ተደርገዋል፡፡ እነዚህ እቅቃሴዎች በአብዛኛው የተመሩትና የተካሄዱት በወጣቶች መሆኑ ከግብጹና ከቱኒዚያው ጋር በባህርይ ያመሳስለዋል፡፡ የዛሬ 20 አመት የወያኔ ጦር በየከተሞች ሊገባ ሲል የተፋለሙት የየከተሞቹ ወጣቶች ነበሩ፡፡ በድንጋይና በዱላ ክላሽን ኮቭ ይተኩሱባቸው የነበሩት የወያኔ ጀሌዎችን የገደሉና ጉሮ ወሸባዬን ያዘፈኑ ወጣቶች ነበሩ፡፡በአምቦ፣ በአረካ፣ በጋምቤላ፣ በሲዳማ፣ በአርባ ምንጭ፣ በሐረር፣ በደብረ ብርሀን፣ በደሴ፣ እንዲሁም በሌሎች ከተሞች የወያኔን ዘረኛና ጎጠኛ መንግስት ተቃውመው የተሰለፉ ያመጹ በአብዛኛው ወጣቶች ነበሩ፡፡ በጎንደር አደባባይ እየሱስ ጸሎት ላይ እንዳሉ በወያኔ ጀሌዎች ተኩስ ተከፍቶባቸው የተገደሉ፣ የቆሰሉ፣ የታሰሩ ወጣቶች ነበሩ፡፡ በአንዋር መስጊድ ሰላት ላይ እንዳሉ ተወረው በአሩምታ ተኩስ የቆሰሉ ብዙ ሲሆኑ አንድ ወጣት መገደሉ የሚታወስ ነው፡፡ ከዚህም በላይ በየዩኒቨርሲቲ ህዝባዊ ጥቄዎችን በማንሳት በርካታ የዩኒቨርሲቲዎች ተማሪዎች በወያኔ ጥይት ተገድዋል፣ ቆስለዋል፣ ተገርፈዋል፣ ትምህርታቸውን አቋርጠው ተሰደዋል፡፡ በየሁለተኛ ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎችም እንደ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች መስዋዕትነትን ተቀብለዋል፡፡ በተናጠል ይካሄድ የነበረው ፀረ-ወያኔ ትግል በ1997 ዓ.ም. በአንድነት በመቆም ወያኔን ያርበተበተ የተቃሞ ሰልፍ ዘጠና ከሙቶው ሰልፈኛ ወጣት የሆነበት ለሀገርና ለወገን ኩራት የሆነ እንቅስቃሴ መደረጉ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው፡፡

ከፊታችን ለተደቀነውና አይቀሬ ለሆነው ህዝባዊ አመጽ ከአሁኑ መደረግ ያለበት ወያኔ እንድንለያይና እርስ በእርሳችን እንዳንተማመን ያሰመረብንን የከፋፍለህ ግዛ መስመር ጥሰን በአንድ ላይ በህብረት ለመቆም ከአሁኑ የህሊና ብቻ ሳይሆን በተግባር የህብረት እንቅስቃሴ መሰረት መጣል ይዋል ይደር አይሉት ግዴታ ነው፡፡ በ1966 ዓ.ም. የሙስሊሙ ህብረተሰብ መብቱን ለማስከበር ባካሄደው ታላቅ ሰላማዊ ሰልፍ ላይ ክርስትያኖችም መሳተፋቸው የማይረሳ አንፀባራቂ የታሪክ አሻራ ነው፡፡ ከነዚህ ከቀድሞዎቹ በህብረትና በጽናት ቆሞ ለነፃነት የመታገልን ታሪክ ዛሬም መድገም አይዘሉት ግዴታ ነውና የሁላችንም አገር ኢትዮጵያ ናትና፣ ሁላችንም ኢትዮጵያውያን ነንና፣ የሀገራችና የእኛም የህዝቦቿ ጠላት ዘረኛው፣ ጎጠኛው፣ ዘራፊውና ቀማኛው አምባ ገነኑ ወያኔ ነውና በአንድ ላይ በጋራ በህብረት እናምጽ!

ድል የእኛ ነው ሞት የእነሱ!